# Learning by Ear 2013

**«መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ—«መዘዙን መቀበል»**

EPISODE 10 « **ከአቅም በላይ**»

**AUTHOR: James Muhando**

**EDITORS: Friederike Müller, Daniel Pelz, Madelaine Meier**

**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of characters by scene:**

**INTRO/OUTRO: NARRATOR**

**SCENE 1: ምህረት AND ትዕግስት TALK**

- **ትዕግስት (F, 15)**
- **ምህረት (F, 15)**

**SCENE 2: ወ/ሮ ሉሊት TALKS TO SEER አቶ መኩሪያ**

- **አቶ መኩሪያ (M, 50’S)**
- **ወ/ሮ ሉሊት (F, 40)**

**SCENE 3: AT THE ሙላቱS’**

- **ብሩክ (M, 8)**
- **ወ/ሮ ሉሊት (F, 40)**
- **ምህረት (F, 15)**
- **ቅዱስ (M, 8)**

**SCENE 4: AT THE HOSPITAL**

- **ብሩክ (M, 8)**
- **ዶ/ር ሮቤል (M, 50’S)**
- **ምህረት (F, 15)**

## INTRO

## 1. NARRATOR:

ጤና ይስጥልን አድማጮች። አሁን የምትከታተሉት «መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ» የተሰኘውን የራዲዮ ድራማ ነው! እስቲ የእስካሁኑን መለስ ብለን እንቃኝ።የምህረት እናት ወ/ሮ ሉሊት ልጃቸው እርጉዝ እንደሆነች አውቀዋል። ይህ ብቻ አይደለም የሚረብሻቸው።የምህረት ሁለት መንትያ ወንድሞች ከላቦሪያ የህፃናት ጉልበት በዝባዥች ለትንሽ ነው ያመለጡት። አባታቸው አቶ ሙላቱ ደግሞ ባላደረጉት የስርቆት ወንጀል ተጠርጥረው አሁንም ፖሊስ ጣቢያ ነው የሚገኙት - እንዲያም ሆኖ ባለቤታቸው ወ/ሮ ሉሊት ለባላቸው ምንም አይነት ሀዘን አይሰማቸውም።

## 2. EPISODE 6, LINES 30 - 32/40:

*ወ/ሮ ሉሊት: አግኝቻታለሁ። ሙላቱ። ልጄን አግኝቼያታለሁ!*

*ሙላቱ: ምህረት ? ጠፍታ ነበር እንዴ?*

*ወ/ሮ ሉሊት: የሸጥካትን ነው እንጂ! ከወራት በፊት የወለድኩት ትንሽዋን ልጄን። ለዛ አቶ መኩሪያ የሸጥካትን ! (…)* **40.** *እዛው እስር ቤት በበሰበስክ!*

## 3. NARRATOR:

ይህ በእንዲህ እንዳለ የወ/ሮ ሉሊት እርጉዝ ልጅ ምህረት ፅንሱን ለማስወረድ ወስና ነበር። ኋላም ጓደኛዋ ትዕግስት ዶክተር ዘሪሁን ጋ ብትወስዳትምበመጨረሻ ሀሳቧን ቀይራለች። ከዛም በኋላ ድንገት ያገንዋት እንግዳ  ሴትዮ ውሳኔዋ ትክክል እንደነበር ነግረዋታል።:

## 4. EPISODE 9, LINES 112-113, 121:

***SAD MOTHER:*** *(…)ልጅት አንድ ነገር ልንገርሽ። ከዛ ክሊኒክ ወጥተሽ መሄድሽ እስከዛሬ ከወሰድሽው ርምጃ ትክክለኛው ነበር።*

*ምህረት :* *እኔንጃ ግራ ተጋብቼያለሁ።… (…)*

***SAD MOTHER (121):*** *ልጄ ምን እንደገጠማት ቆይ ልንገርሽ…….*

**5. NARRATOR:**

ይህ «ከአቅም በላይ» የተሰኘው 10ኛው ክፍል ነው። በሚቀጥለው ቀን ምህረት እና ትዕግስትን ትምህርት ቤት ውስጥ በዕረፍት ሰዓት እናገኛቸው። …

**<u>SCENE 1: ምህረት AND ትዕግስት TALK</u>**

**6. ATMO: BONGO ACADEMY AT BREAK, OUTSIDE**

**7. SFX: SCHOOL BELL**

**8.** ትዕግስት: **(from far)** ምህረት ፣ምህረት! ጠብቂኝ!

**9. SFX:** ትዕግስት **RUNNING TOWARDS** ምህረት

**10.** ምህረት **:** **(shortly)** ትዕግስት የሚቀጥለው ትምህርት እንዳያመልጠን።

**11. SFX: OUTSIDE ATMO GRADUALLY GETS QUIET AS STUDENTS GO BACK TO CLASS**

**12.** ትዕግስት**:** ትናንት ምንድን ነው እንደዛ ያስፈረጠጠሽ?

**13.** ምህረት **:** ላደርገው አልቻልኩም ነበር።

**14.** ትዕግስት: ግፋ ቢል 30 ደቂቃ እኮ ነበር የሚፈጀው። ተመልሰሽ መሄድ አለብሽ።

**15.** ምህረት : ፅንሱን ላለማስወረድ ወስኛለሁ።

***KW BEGIN***

**16.** ትዕግስት: **(desperate)** ምን? ምህረት ? የዳንኤልስ ጉዳይ? ተመልሶ አብሮሽ ለመሆን የፈለገ መስሎኝ?

**17.** ምህረት : ዳንኤል አያፈቅረኝም። ከኔ የሚፈልገው ነገር ቢኖር ፅንሱን እንዳስወርድ ነው። ስለዚህ የገጠመኝን ችግር የግዴታ ከኔ ጋ መጋፈጥ የለበትም።

**18.** ትዕግስት: ትምህርትሽስ? ሆድሽ በቅርቡ ማበጥ ይጀምራል። ርዕሰ መምህርት ሰብለ ደግሞ ይህንን ካወቁ ያባርሩሻል።

**19.** ምህረት : **(shouts)** ትዕግስት ወስኛለሁ። በቃ አለቀ!

***KW END***

**20.** ትዕግስት: **(trying to convince her)** ግን ምህረት ስላንቺ አስቤ ነው። በኋላ ህይወትሽ--

**21.** ምህረት : አቁሚ! በእናትሽ አቁሚ ብዬሻለሁ። ግን ለምንድን ነው ሁሉም ሰው የሚዋሽኝ?

**22.** ትዕግስት: ምንድን ነው የምትዩው?

**23.** ምህረት : የማላውቅ መሰለሽ? ዶክተር ዘሪሁን ጋ ከነበሩት ሴትዮ ጋ አውርቻለሁ እኮ። ምን እንዳሉኝ ታውቂያለሽ?

**24.** ትዕግስት: ያቺ እብድ ሴትዮ? ከመቼ ጀምሮ ነው እብድ የሚለውን የምትሰሚው?

**25.** ምህረት : **(ignoring her)** ልጃቸውን እንድታስወርድ ዶክተር ዘሪሁን ጋ ልከዋት ነበር ። ኋላ ግን ልጃቸው ሞተች። ሌላ ደግሞ ምን እንደነገሩኝ ልንገርሽ?! ዶክተር ዘሪሁን –ደንበኞች እንዲያመጡለት ወጣት ሴቶችን ትንሽ አበል እየከፈለ ይጠቀምባቸዋል።

**26.** ትዕግስት: **(gasps)**

**27.** ምህረት : ሴትየዋም በሰው ተታለው ነው ልጃቸውን ወደዛ የላኳት።

**28.** ትዕግስት: ምህረት – ዶክተር ዘሪሁን በጣም ጎበዝ ሀኪም ነው። አንቺ ደግሞ፤ ሴትየዋ ባክሽ እብድ ናት። --

**29.** ምህረት : አቁሚ ትዕግስት። አንድና አንድን መደመር አያቅተኝም። አንቺ ፅንሱን እንዳስወርድ እና ዶክተር ዘሪሁን ጋ እንድሄድ ስትመክሪኝ ነበር። ይህንንም ያደረግሽው ደንበኛ ስታመጪለት ገንዘብ ስለሚከፍልሽ ነው።

**30.** ትዕግስት: ምህረት የምትናገሪውን አታውቂም፤ ማስወረድ እኮ--

**31.** ምህረት : **(shouts, interrupts her)** *በቃ ሂጂ* ትዕግስት! ሂጂልኝ! ከአሁን በኋላ ዳግም ላይሽ አልፈልግም።

**32.** ትዕግስት: **(snaps)** ጥሩ እኔን ማየት ካልፈለግሽ ክፍል ስንገባ አይንሽን ጨፍነሽ ቆዩኝ እሺ።

***KW BEGIN***

**33. ምህረት :** ይህን ያህል ጊዜ ጓደኛዬ መስለሽ ለካ እንዲህ ስ ታስመስይ ነበር። ልንገርሽ፤ አንቺ ግን የለየላት ደም መጣጭ ነገር ነሽ።

**34. SFX: FOOTSTEPS AS ምህረት LEAVES**

**35. ትዕግስት:** ጥሩ! ይህንን የሰይጣን ቁራጭ በሆድሽ ታቀፊ ምን ቸገረኝ። **(to herself)** ቆይ ብቻ ግን ያሳጣሽኝን ገንዘብ እና በዶክተር ዘሪሁን ፊት ያዋርድሽኝን ባለስተፋሽ ምን አለች በዪኝ። ጠብቂኝ ብቻ ምህረት ሙላቱ…

***KW END***

**36. MUSICAL INTERLUDE**

<u>**SCENE 2: ወ/ሮ ሉሊት TALKS TO SEER ባለውቃቢ መንገሻ**</u>

**37. ATMO: QUIET NEIGHBOURHOOD; EVENING, BIRDS CHIRPING**

**38. SFX: CALABASH FILLED WITH SEEDS BEING SHAKEN**

**39. ባለውቃቢ መንገሻ:** **(chants in strange language as he shakes the calabash)**

**40. SFX: FOOTSTEPS (SHOES) APPROACHING ON EARTH FLOOR**

**41. ወ/ሮ ሉሊት:** **(timidly)** ሰላም! ወ/ሮ ሉሊት እባላለሁ…

***KW BEGIN***

**42.** ባለውቃቢ መንገሻ: **(scary voice)** እዛው ቁሚ። እኮ ማነው የመንገሻ የታዋቂው ባለውቃቢ ቤት ጫማ ሳያወልቅ ዘው ብሎ ለመግባት የሚደፍረው?

**43.** ወ/ሮ ሉሊት: ይቅርታ ጌታዬ መንገሻ …

**44.** ባለውቃቢ መንገሻ: ጫማሽን አውልቀሽ ፊትሽን ዙረሽ ግቢ

**45.** ወ/ሮ ሉሊት: ይሁና እርስዎን ምን ይሳንዎታል።

**46. SFX: SHOES REMOVED**

**47. SFX: FOOTSTEPS BAREFOOT ON EARTH FLOOR**

**48.** አቶ መኩሪያ: ፊትሽን ዙሪ እና ተቀመጭ

**49. SFX: CLOTHES RUSTLE AS SHE SITS**

**50.** ባለውቃቢ መንገሻ: አጠገብሽ ያለው ድንጋይ ላይ ሳንቲም አስቀምጪ

**51. SFX: COIN PUT ON STONE**

**52.** ወ/ሮ ሉሊት: እንደነገርኩዎ ስሜ ወ/ሮ ሉሊት ነው…

***KW END***

**53.** ባለውቃቢ መንገሻ: **(cuts in roughly)** ማን እንደሆንሽ አውቃለሁ! መንገሻ ሁሉንም ነገር ነው የሚያውቀው። እሺ እዚህ ምን አመጣሽ ወ/ሮ ሉሊት?

**54.** ወ/ሮ ሉሊት: ውይ ጌታዬ ትንሽ ብርሃን ቢጤ እንደው? እ.. እይ… አይታዩኝም!

**55. SFX: AGGRESSIVE CALABASH SHAKING**

**56.** ባለውቃቢ መንገሻ: እንዴት ደፋር ነሽ? መንገሻ  በደንብ ያይሻል። አሁን ችግርሽን ተናገሪ። ታላቁ ሰው እንዲህ እንደዋዛ የሚያበክነው ሰዓት የለውም።

**57.** ወ/ሮ ሉሊት: **(shyly)** የ… የኔ ችግር ብዙ ነው ከየት እንደምጀምርልዎ አላውቅም። ባለቤቴ ህፃኗን ልጄን ሸጧታል። … እና ልጄ እንድትመለስልኝ እፈልጋለሁ።

**58.** ባለውቃቢ መንገሻ: **(shakes calabash)** አሀ!! የባል ችግር፤ እሺ ቀጥይ።

**59.** ወ/ሮ ሉሊት: ሌላኛዋ ሴት ልጄ ነፍሰ ጡር ናት። ሁለቱ  ወንድ ልጆቼ ደግሞ ታመዋል። የሚሻላቸውም አይመስልም።

**60.** ባለውቃቢ  መንገሻ: እእእ … ነፍሰ ጡር ልጅ … የታመሙ ልጆች … ምን ያህል ነው ያመማቸው?

**61.** ወ/ሮ ሉሊት: ብሩክ ሳሉ አላቆም ብሎታል ቅዱስ ደግሞ ያቃዠዋል።

***KW BEGIN***

**62.** ባለውቃቢ መንገሻ: **(exaggerated chanting)** በጣም የሚያሳዝን ነው። መናፍስቱ የሚነግሩኝ ወንዶቹ ልጆችሽ ዛር ስለያዛቸው በቅርቡ እንደሚሞቱ ነው።

**63.** ወ/ሮ ሉሊት: **(weeps)**ውይ!  ወይኔ ጉዴ! ልጆቼን! እባክዎን ሊረዱኝ አይችሉም?

***KW END***

**64.** ባለውቃቢ መንገሻ: **(chants)** መናፍስቱ ሁለት ነጭ አውራ ዶሮች እና 4 እንቁላል እንድታመጪ ይላሉ።

**65.** ወ/ሮ ሉሊት: ግን ገንዘብየለኝም ለመክፈ --

**66.** አቶ መንገሻ: **(shouts)** ፀጥታ! **(chants)** የኔ ልጅ እድለኛ ነሽ። መናፍስቱ ዛሬ ጥሩ ስሜት ላይ ናቸው። እንግዲያውስ ነገ አንድ ነጭ ቄብ ዶሮ እና ሁለት እንቁላል እንድታመጪ ይሁን።

**67.** ወ/ሮ ሉሊት: እሺ አመሰግናለሁ። ደግ፤ አመሰግናለሁ።...

**68.** ባለውቃቢ መንገሻ: ለአሁኑ እንኪ ይሄንን ዱቄት ውሰጂ። በሰስ ላስቲክ ውስጥ አከትልሻለሁ።

**69. SFX: SOMETHING BEING WRAPPED IN PLASTIC BAG**

**70.** ባለውቃቢ መንገሻ: ልጆችሽ ግንባር ላይ ለሊት ለሊት ነሽኒሽላቸው። እርኩስ መንፈስን ያርቅላቸዋል።

**71.** ወ/ሮ ሉሊት: የህፃኗስ ነገር? ፖሊስ ጉዳዩን እየተከታተልን ነው ብሎኝ ነበር። ልጄ ትመለስልኛለች ማለት ነው?

**72.** ባለውቃቢ መንገሻ ነገ ተመለሽ አልኩሽ እኮ! አሁን ፊትሽን አዙሪ እና ውጪ። ወደኋላ ብዬ እያለሁ ብትይ ድንጋይ ሆነሽ ነው የምትቀሪው።

**73.** ወ/ሮ ሉሊት: እሺ እሺ። መጀን በእርስዎ! ምን ይሳንዎዋል።!

**74. SFX: FOOTSTEPS - ወ/ሮ ሉሊት GOING AWAY**

**75.** ባለውቃቢ መንገሻ: **(resumes chanting)**

**76. MUSICAL INTERLUDE**

**SCENE 3: AT THE ሙላቱS’**

**77. SFX: NIGHT ATMO IN TANDIKA SLUMS – INTERIOR**

**78. ብሩክ: UNCONTROLLABLE COUGHING AND WHEEZING**

**79. ወ/ሮ ሉሊት:** **(asleep, breathing deeply)**

***KW BEGIN***

**80. ቅዱስ:** ምህረት ፣ ምህረት ! እስኪ ነቃ በይ! ብሩክ ሳሉ ሊቆምለት አልቻለም። አየር አጥሮታል።

**81. ምህረት :** **(sleepily)** ምን? ብሩክ ወይኔ ወንድሜ ምን ሆነ? ቅዱስ እባክህ አጠገብህ ያለውን የክብሪት ቤት አቀብለኝ።

**82. SFX: MATCHBOX PASSED**

**83. ብሩክ:** **(coughs, weakly)** እማዬን ጥሯት

**84. ምህረት :** ቆይ ብሩክ አንዴ ኩራዙን ላብራ…

**85. SFX: MATCHSTICK STRUCK AND LANTERN LIT**

**86. ብሩክ:** **(coughs)**

**87. ቅዱስ:** ወይኔ ምህረት ተመልከች! ወንድማችን ደም እየተፋ ነው። ሊሞትብን ነው ማለት ነው?!

**88. ምህረት :** እሸሸሸ! እንደሱ አትበል ቅዱስ። ይሻለዋል።

***KW END***

**89. SFX: ምህረት SHAKES HER MOTHER**

**90.** ምህረት : **(whispering urgently)** እማ! ተነሽ፤ እማ!

**91.** ወ/ሮ ሉሊት: **(sleepily)** ምንድን ነው ምህረት?

**92.** ምህረት : እማ ብሩክ ደም እያስተፋው ነው።

**93. SFX: BED CREAKING AS ወ/ሮ ሉሊት WAKES**

**94.** ወ/ሮ ሉሊት: **(panics)** ወይኔ ጉዴ ፍጠኝ ምህረት። እዛ ምድጃው አጠገብ ያለውን ላስቲክ አቀብይኝ!

**95. SFX: PLASTIC BAG PASSED AND OPENED**

**96.** ወ/ሮ ሉሊት: ይኼ ሀይል ይረዳሀል ብሩክ። ሁሉም ነገር ደህና ይሆናል። ታላቁ ባለውቃቢ ሁሉም ነገር ጥሩ እንደሚሆን ነግረውኛል።

**97.** ምህረት : እማዬ! ምንድን ነው ይኼ ብሩክ ጭንቅላት ላይ የምትነሽንሽው የገማ ሽታ ያለው አቧራ?

**98.** ወ/ሮ ሉሊት: መንገሻየሰጡኝ መድሀኒት ነው። ታላቁ ፈውሰኛ።

**99.** ምህረት : ምን?! አቶ መንገሻ ፈውሰኛ አይደሉም። እማዬ! አጭበርባሪ ናቸው።

**100.** ወ/ሮ ሉሊት: የት የምታውቂውን ነው?! ይልቁንስ ማንቆርቆሪያው ውስጥ ያለውን ውሃ ከሎሚ ጋ አርገሽ አቀብይኝ።

**101.** ምህረት : እማዬ! እንደሚመስለኝ ብሩክን ወደ ሆስፒታል ብንወስደው ይሻላል።

**102.** ወ/ሮ ሉሊት: **(strict)** አቅማችን አይፈቅድም። ገና ባለውቃቢውን መክፈል አለብኝ።

**103.** ምህረት : ግን እማዬ በእውነት እኛ --

**104.** ወ/ሮ ሉሊት: **(shouts)** አፍሽን ዝጊና ያልኩሽን አድርጊ። ውሃ በሎሚውን ስጪኝ።

**105. SFX: WATER POURED IN CUP**

**106.** ወ/ሮ ሉሊት: ይህንን ጠጣ ብሩክ ጠጣ!

**107.** ብሩክ: **(drinks, cough subsides)**

**108.** ወ/ሮ ሉሊት: ተኛትበት እስኪ ልጄ፤ ተኛበት።

**109. MUSICAL INTERLUDE**

## SCENE 4: AT THE HOSPITAL

**110. SFX: HOSPITAL ATMO, (KIDS CRYING, COUGHING ETC, HEARD THROUGH DOOR)**

**111.** ምህረት : አይዞህ ብሩኬ አሁን ይሻልሃል።

**112.** ብሩክ: **(coughing)** ምህረት ለምንድን ነው እንዲህ በጠዋት ወደ ሆስፒታል የመምጣነው? እማዬንስ አብራን እንድትመጣ ለምን አልቀሰቀሻትም?

**113.** ምህረት : እሽሽሽ አይዞህ ወንድሜ – ብዙ ላለማውራት ሞክር

**114.** ብሩክ **(more coughing)**

**115. SFX: STEPS ዶ/ር ሮቤል ENTERS**

**116. SFX: DOOR CLOSING**

**117.** ዶ/ር ሮቤል: እንደምን ናችሁ። ዶ/ር ሮቤል እባላለሁ። እዚህ ሆስፒታል ነው የምሰራው።አንተ ብሩክ ሙላቱ መሆን አለብህ?

**118.** ብሩክ: **(amid coughs, shyly)** አዎ!

***KW BEGIN***

**119.** ዶ/ር ሮቤል: አንቺስ? እናቱ ነሽ?

**120.** ምህረት : **(embarrassed)** አይ አይ። ምህረት እባላለሁ። ብሩክ ወንድሜ ነው።

**121.** ዶ/ር ሮቤል: ወጣት ስለሆንሽ እኔም ገርሞኝ ነበር።…ታዲያ በአሁን ሰዓት ትምህርት ቤት መሆን አልነበረብሽም እንዴ?

**122.** ምህረት : ከዚህ በኋላ ት/ቤት እሄዳለሁ።

**123.** ዶ/ር ሮቤል: ወላጆቻችሁ የት ሄደው ነው?

**124.** ምህረት : **(avoiding)** እእ… መምጣት ስላልቻሉ ነው። … እባክዎን ዶ/ር ሮቤል ወንድሜን ሊመረምሩት ይችላሉ? የሆነው ነገር በጣም ነው ያስጨነቀኝ።

**125.** ዶ/ር ሮቤል: በሚገባ!

**126.** ብሩክ: **(tries to say something but coughs instead)**

***KW END***

**127.** ምህረት :
ዶክተር ወንድሜ ሳሉ ሊለቀው አልቻለም። ባለፈው ሌሊት ደም ሲያስተፋው ነበር። ለዛ ነው ዛሬ ጠዋት እርሶ ዘንድ ያመጣነው።

**128.** ዶ/ር ሮቤል:
ከሳሉ ባሻገርስ ሌሊት ሌሊት ጥሩ እንቅልፍ ይተኛል?

**129.** ምህረት :
አይ። ሁሌ እንዳላበው ነው። ቀዝቃዛ ሆኖ እንኳን በላብ ይዘፈቃል። የኛ ቤት ደግሞ ሌሊት ላይ በጣም ይቀዘቅዛል።

**130.** ዶ/ር ሮቤል:
ወንድምሽ በጣም ቀጫጫ ነው። ምግብስ በሚገባ ይመገባል?

**131.** ምህረት :
አይ አሁን ትቷል። በፊት ብዙ ይበላ ነበር። አሁን አሁን ግን ምግቡን ይቀምስና ይተወዋል። ክብደቱም ቀንሷል። እናቴ ደግሞ የሆነ መጥፎ ሽታ ያለው የቅጠላ ቅጠል ዱቄት ሰጠችው። ግን እንደሚመስለኝ ትክክለኛ መድሀኒት ያስፈልገዋል ።

**132.** ዶ/ር ሮቤል:
ለባህል መዳህኒቶች ከፍተኛ አክብሮት ነው ያለኝ። ግን በዚህ ሁኔታ ወንድምሽን ይዘሽው  መምጣትሽ ትክክል ነበር። ስንት ጊዜ ሆነው?

**133.** ምህረት :
እሱ እና ወንድሜ ከላቦሪያ ከተመለሱ ጊዜ አንስቶ ነው።

**134.** ዶ/ር ሮቤል:
ላቦሪያ? እእእ...እንደዚህ አይነት ምልዕክቶች የሚታዩት ሰዎች ተሰባስበው በሚኖሩበት አካባቢ ነው። ወይንም ደግሞ ለምሳሌ የማዕድን ማውጫ የሚሰሩ ሰዎች ላይ ነው። ግን ወንድምሽ ያን ለማድረግ ገና ለጋ ልጅ ነው። ... ለማንኛውም – እዚህ ድረስ ማምጣትሽ ልክ ነበር ምህረት። ትንሽ የምፈራው ይህ ነገር አደገኛ እንዳይሆን ነው።

## 135. OUTRO – NARRATOR:

**የምህረት ወንድም ብሩክ ምን ሆኖ ይሆን? የሚቀጥለው ጊዜ ሬዲዮናችሁን ክፈቱና ተከታተሉን። ይህንን ጭውውት ደግማቹህ ለመስማት ከፈለጋቹህ ድረ ገፃችን dw.de/lbe ን ጎብኙ። ፌስ ቡክ ላይም ልትከታተሉን ትችላላችሁ። አስተያየታችሁን መስማት ደስ ይለናል። እስከዛው። ደና ቆዩን።**